ሠላሳ ስድስተኛ ዓመት ቊጥር ፴
36th Year — No. 30

አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፩ ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ. ም.
Addis Ababa, 27th August, 1977

የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት

ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ።
NEGARIT GAZETA

የጋዜጣው ፡ ዋጋ ፤
ባገር ፡ ውስጥ ፡ ባመት ፡ 6 ብር
» » በ፮ ፡ ወር ፡ 3 ብር
» » ያንዱ ፡ ½ ብር

በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢ
ጽሕፈት ቤት ተጠባባቂነት የወጣ

ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይታተማል

የፖስታ ሣጥን ቊጥር ፩ሺ፴፩ (1031)

ማ ው ጫ
፲፱፻፷፱ ዓ. ም.

አዋጅ ቊጥር ፩፻፳፱/፲፱፻፷፱ ዓ. ም.
የብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ
አዋጅ . . . . ገጽ ፪፻፹፯

CONTENTS
1977

Proclamation No. 129 of 1977
National Revolutionary Operations
Command Proclamation . . . . Page 287

አዋጅ ቊጥር ፩፻፳፱/፲፱፻፷፱ ዓ. ም.

የብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

« ኢትዮጵያ ትቅደም »

የመስፋፋት ፍላጎት ያለው አድኃሪ የጎረቤት የገዢ መደብ ጠንካራና አብዮታዊት ኢትዮጵያን ለማየት የማይፈልጉ የውስጥና የውጭ አድኃሪ ኃይሎች በኢምፔሪያሊዝም አቀነባባሪነት ዳር ድንበራችን እንዲደፈር ፤ አንድነታችን እንዲፈርስና አብዮታችን እንዲቀለበስ ከዚህም አልፎ ሕልውናችን እንዲጠፋ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ከፍተኛ ከበባና ወረራ በማድረግ ላይ ስለሆኑ ፤

እነኝህን ጠላቶችና ፀረ አንድነትና ፀረ አብዮት ድርጊቶች ለመቋቋም ሰፊውና አገር ወዳዱ ሕዝብ ሕይወቱንና ንብረቱን በመስጠት የሚያደፋፍሩና የሚያኮሩ ጥረቶችን እያደረገ ፤ እርምጃዎችንም እየወሰደ ቢሆንም ትግሉ በአጭር ጊዜ ሳይወሰን መራራና ረጅም በመሆኑ ጠላቶቻችንን ለመደምሰስ የምናደርገው ዝግጅት ጠንካራና የተቀነባበረ መሆን ስላለበት፤

በተጨማሪም ድኅነትና የኢኮኖሚ ጥገኝነት ከእነዚህ ጠላቶች ተለይተው የማይታዩ በመሆናቸው የአብዮታዊት እናት አገራችን ኢኮኖሚ እንዲዳብርና ምርት እንዲያድግ የልማት ሥራዎችንና እንቅስቃሴዎችን ከመቼውም ይበልጥ በማስፋፋትና በማካሔድ በእነዚህም ላይ ዘመቻ ማድረግ ተገቢ ስለሆነ ፤

ከላይ የተመለከቱትን ለመፈጸም መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች አሠራራቸውና አቋማቸው ፤ እንደዚሁም የሰፊውና የአገር ወዳዱ ሕዝብ ተሳትፎ የተቀነባበረ ፈር እንዲይዝ ማድረግ አስፈላጊ ስለሆነና ይህንንም ከግብ ለማድረስ ተገቢው ሥልጣን ያለው በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሊቀ መንበር የሚመራ ብሔራዊ አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ ማቋቋም ስላስፈለገ ፤

PROCLAMATION No. 129 OF 1977

A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF A NATIONAL REVOLUTIONARY OPERATIONS COMMAND

"ETHIOPIA TIKDEM"

WHEREAS, the reactionary ruling class of a neighbouring country with its expansionist policy, and the reactionary internal and external forces that hate to see a strong and revolutionary Ethiopia are, with the backing of imperialism, more than ever before, encircling and invading our country with a view to violating our territorial integrity, unity and threatening our very existence and our Revolution;

WHEREAS, though the broad masses and patriots are making encouraging and commendable efforts in combatting the enemies and in taking exemplary measures against anti-unity and anti-revolutionary elements by providing their property and sacrificing their lives, to carry out the struggle which is expected to be bitter and protracted, it is necessary to strengthen and coordinate our efforts and preparations;

WHEREAS, poverty and economic dependence cannot be seen in isolation from the enemies mentioned above, it is necessary to fight them by increasing production and enhancing development works for the purpose of improving the economy of our Revolutionary Motherland;

WHEREAS, it is necessary to establish a National Revolutionary Operations Command headed by the Chairman of the Provisional Military Administration Council and vested with the necessary powers and duties to coordinate the set-up and working procedures of government offices and mass organizations and the participation of the broad masses and patriots which is essential to achieve the goals set out above;

ECLN
http://www.ethcriminalawnetwork.com/

የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግንና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ሥልጣንና ኃላፊነት እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩፻፲/፲፱፻፷፱ ዓ. ም. አንቀጽ ፭ (፮) መሠረት ከዚህ የሚከተለው ታውጇል ።

ምዕራፍ ፩ ጠቅላላ ፤

፩ ፤ አጭር ርእስ ፤

ይህ አዋጅ «የብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፳፱/፲፱፻፷፱ ዓ. ም.» ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል ።

፪ ፤ ስለብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ መቋቋም ፤

፩/ ከዚህ በታች የተመለከቱት ተግባርና ሥልጣን ያሉት በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሊቀ መንበር የሚመራ ብሔራዊ አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል ።

፪/ የብሔራዊ አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ የራሱ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል ። ጽሕፈት ቤቱ በመምሪያው መመሪያና ትእዛዝ መሠረት አዛዦቹንና በማዕከላዊ ደረጃ የሚቋቋሙትን የድጋፍ ኮሚቴዎች ፤ ያለውን የሰው ፤ የገንዘብና የቁሳቁስ ኃይል ፤ እንደዚሁም የሚያስፈልጉትን ሌሎች ዝግጅቶች የሚያስተባብር የመምሪያውን ትእዛዞች የሚያስተላልፍና ውሳኔዎቹ መፈጸማቸውን የሚያረጋግጥ በመንግሥት የሚሾም ኃላፊ ይኖረዋል ።

፫ ፤ ብሔራዊ አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ አቋም ፤

ብሔራዊ አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ ፤

፩/ የዘመቻ ጉባኤ ፤
፪/ እዞች ፤
፫/ የእዝ ቀጠና የዘመቻ ጉባኤ ፤
፬/ የክፍለ አገር የአብዮት የዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ
፭/ የአውራጃ የአብዮት የዘመቻ » »
፮/ የወረዳ የአብዮት የዘመቻ » » እና
፯/ የአዲስ አበባ የአብዮት የዘመቻ » »

ይኖሩታል ።

ምዕራፍ ሁለት ፤

ስለብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያና ስለብሔራዊ የዘመቻ ጉባኤ

፬ ፤ የብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ ተግባርና ሥልጣን ፤

ብሔራዊ አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ የሚከተሉት ተግባርና ሥልጣኖች ይኖሩታል ፤

፩/ በአገሪቱ አንድነትና ነፃነት ፤ እንደዚሁም በአብዮት ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ለመከላከል ሁኔታውን በመገምገም መደበኛው ጦር ፤ የፖሊስ ሠራዊትና ሕዝባዊው ሠራዊት እንዲንቀሳቀስ አስፈላጊውን ትእዛዝና ውሳኔ የመስጠት ፤

፪/ ስለአገሪቱ አንድነትና ስለአብዮቱ ጥበቃ ሕዝቡ ተካፋይ እንዲሆን አስፈላጊውን መመሪያና ትእዛዝ ለዕዞች ፤ ለሚመለከታቸው ሚኒስትሮች ፤ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ሕዝባዊ ድርጅቶች የመስጠት ፤

፫/ የአጭርና የረጅም ጊዜ የመከላከያ የዘመቻ ዕቅድ የማዘጋጀት ፤ ዘመቻውን በበላይነት የመምራት ፤ የመቆጣጠር ፤ የመከታተል ፤

NOW THEREFORE, in accordance with Article 5 (6) of the Redefinition of the Powers and Responsibilities of the Provisional Military Administration Council and the Council of Ministers Proclamation No. 110/1977, it is hereby proclaimed as follows:

Chapter One
GENERAL

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "National Revolutionary Operations Command Proclamation No. 129/1977."

2. *Establishment of the National Revolutionary Operations Command*

1) There is hereby established a National Revolutionary Operations Command that is headed by the Chairman of the Provisional Military Administration Council which shall have the powers and duties specified in this Proclamation.

2) The National Revolutionary Operations Command shall have its own office. The office shall be headed by a person to be appointed by the Government who shall, in accordance with the directives of the Command, coordinate the Sector Commands and the support committees established at the central level, the man-power, financial and material resources and other necessary facilities, transmit the orders of the Command and ensure the implementation of its decision.

3. *Organization of the National Revolutionary Operations Command*

The National Revolutionary Operations Command shall be composed of the following organs:

1) The Operations Council;
2) Sector Commands;
3) Sector Command Operations Council;
4) Regional Revolutionary Operations Coordinating Committee;
5) Awraja Revolutionary Operations Coordinating Committee;
6) Woreda Revolutionary Operations Coordinating Committee; and
7) Addis Ababa Revolutionary Operations Coordinating Committee;

Chapter Two
NATIONAL REVOLUTIONARY OPERATIONS COMMAND AND NATIONAL OPERATIONS COUNCIL

4. *Powers and Duties of the National Revolutionary Operations Command*

TheNational Revolutionary Operations Command shall have the following powers and duties:

1) to evalute the situation with a view to repelling the aggression against the unity and independence of the country and the Revolution and issue the necessary orders and decisions for the mobilization of the regular army, the police and the militia;

2) to issue to the sector commands, the appropriate ministries, and other government offices and mass organizations instructions and orders relating to the participation of the people in defense of the unity of the Country and the Revolution;

3) to prepare short and long term defense and operations plans; be responsible for the overall direction, supervision and follow-up of the operations;

ECLN

http://www.ethcriminalawnetwork.com/

፬/ አስፈላጊ የሆኑትን የድጋፍ ኮሚቴዎች በማዕከላዊ ደረጃ የማቋቋም ፤

፭/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፫ ለተመለከቱት ጉዳዮች ተገቢውን መመሪያ የመስጠት ፤

፭ ፤ የብሔራዊ የዘመቻ ጉባኤ አባሎችና ስብሰባ ፤

፩/ የብሔራዊ የዘመቻ ጉባኤ የሚከተሉት አባሎች ይኖሩታል ፤

ሀ) የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሊቀ መንበር .... ሰብሳቢ

ለ) የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ምክትል ሊቀ መንበር ...... ምክትል ሰብሳቢ

ሐ) የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ዋና ጸሐፊ .... አባል

መ) የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የወታደራዊ ፖለቲካ ጉዳይ ኃላፊ . . . . አባል

ሠ) የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የመከላከያ ጉዳይ ኃላፊ . . . . አባል

ረ) የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የሕዝብ ደኅንነት ጉዳይ ኃላፊ . . . . . . አባል

ሰ) ተቀዳሚ ሚኒስትር . . . . »

ሸ) የአገር መከላከያ ሚኒስትር . . . . . . »

ቀ) የአገር አስተዳደር ሚኒስትር . . . . . »

በ) የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር . . . . . . »

ተ) የማስታወቂያና መርሐ ብሔር ሚኒስትር . . »

ቸ) ኢታ ማጀር ሹም . . . . »

ኀ) የምድር ጦር አዛዥ . . . . »

ነ) የአየር ኃይል አዛዥ . . . . »

ኘ) የባሕር ኃይል አዛዥ . . . . »

አ) የፖሊስ ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ . . . . »

ከ) የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት አባሎች ፭ .... »

ኸ) የመ. ኢ. ሠ. ማ. ሊቀ መንበርና ምክትል ሊቀ መንበር . . . . »

ወ) የአርበኞች ማኅበር ሊቀ መንበር . . . »

ዐ) የሴቶች ድርጅት ተወካይ . . . . . »

ዘ) የወጣቶች ድርጅት ተወካይ . . . . . »

ዠ) የገበሬ ማኅበራት ፪ ተወካዮች . . . . . »

፪/ የጉባኤው አባሎች በ፲፭ ቀን አንድ ጊዜ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ይሰበሰባሉ ።

፮ ፤ የብሔራዊ የዘመቻ ጉባኤ ተግባርና ሥልጣን ፤

የብሔራዊ የዘመቻ ጉባኤ የሚከተሉት ተግባርና ሥልጣን ይኖሩታል ።

፩/ ከብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ የሚሰጠውን መግለጫና መመሪያ እንደሁኔታው ለሚወክላቸው ድርጅቶች የማሳወቅ ፤ ከድርጅቶች ስለዘመቻው የሚቀርቡትን ሐሳቦች ለብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ የማቅረብ ፤

፪/ ዘመቻው በተሳካ ሁኔታ እንዲራመድና ግቡን እንዲመታ ለብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ ሐሳብ የማቅረብ ፤

፫/ በዘመቻው ምክንያት በኅብረተሰቡ ሊደርሱ የሚችሉትን የኢኮኖሚ ፤ የማኅበራዊ ጉዳይና የፖለቲካ ቀውሶች የሚስተካከሉበትን መንገድ የመጠቆም ፤

4) to establish the necessary support committees at the central level; and

5) to issue directives concerning matters specified under Article 23 hereof.

5. *Composition and Meetings of the National Operations Council*

1) The National Operations Council shall have the follwing members:

a) the Chairman of the Provisional Military Administration Council .... Chairman

b) the Vice-Chairman of the Provisional Military Administration Council... Vice-Chairman

c) the Secretary General of the Provisional Military Administration Council .... Member

d) member of the Provisional Military Administration Council in charge of military political affairs .... "

e) member of the Provisional Military Administration Council in charge of defence affairs .... "

f) member of the Provisional Military Administration Council in charge of public safety affairs .... "

g) the Senior Minister .... "

h) the Minister of National Defence ... "

i) the Minister of Interior .... "

j) the Minister of Foreign Affairs .... "

k) the Minister of Information and National Guidance .... "

l) the Chief of Staff .... "

m) the Commander of the Ground Force "

n) the Commander of the Air Force ... "

o) the Commander of the Navy ...... "

p) the Police Commissioner .... "

q) five members of the Provisional Office for Mass Organizational Affairs .... "

r) the Chairman and Vice-Chairman of the All Ethiopia Trade Union .... "

s) the Chairman of the Patriots' Association .... "

t) a representative of the Women's Association .... "

u) a representative of the Youth Association .... "

v) two representatives of Peasant Associations .... "

2) The Council shall meet once in 15 days or as may be necessary.

6. *Powers and Duties of the National Operations Council*

The National Operations Council shall have the following powers and duties:

1) to transmit reports and directives it receives from the National Revolutionary Operations Command to all organizations it represents and to transmit to the National Revolutionary Operations Command suggestions on the operations from the organization;

2) to give policy guidelines to the National Revolutionary Operations Command on the successful conduct of the operations and the achievement of its goal;

3) to submit proposals on ways of solving the economic, social and political dislocations of the society arising from the operations.

ECLN

http://www.ethcriminalawnetwork.com/

፬/ አብዮቱንና የአገሪቱን አንድነት ለመጠበቅ በየጊዜው በጦር ግንባር ለሚሠለፉ ኃይሎች የሚፈለገውን የገንዘብ ፤ የሞራልና የልዩ ልዩ እርዳታዎች ድጋፍ ማስተባበር ፤ ድጋፉ በየጊዜው ከፍ እንዲል የማያቋርጥ ጥረት የማድረግ ፤

፭/ የኢትዮጵያ አብዮት የተቀዳጃቸው ድሎች እንዲከበሩና እንዲጠናከሩ ፤ እንዲሁም የአገሪቷ ዳር ድንበርና ነፃነት እንዲከበር ሰፊውን ሕዝብ የመቀስቀስና የማስተባበር ።

ምዕራፍ ሦስት ፤

ስለእዞችና ስለእዞች የዘመቻ ጉባኤ

፯ ፤ እዞች ፤

፩/ በአገሪቱ አንድነትና በአብዮቱ ላይ የተሠነዘረውን ወረራና ከበባ ለመከላከልና ለመደምሰስ እንዲያስችል የሕዝቡንም አብዮታዊ ተሳትፎ በተቀነባበረ ሁኔታ ለመምራት የሚከተሉት ፭ ዕዞች ተቋቁመዋል

ሀ) የማዕከላዊ እዝ ፤
- ፩/ አዲስ አበባ
- ፪/ ሸዋ ክፍለ ሀገር
- ፫/ አርሲ ክፍለ ሀገር
- ፬/ ወሎ ክፍለ ሀገር
- ፭/ ጐጃም ክፍለ ሀገር

ለ) የሰሜን እዝ ፤
- ፩/ ትግራይ ክፍለ ሀገር
- ፪/ ኤርትራ ክፍለ ሀገር
- ፫/ ጐንደር ክፍለ ሀገር

ሐ) የምዕራብ እዝ ፤
- ፩/ ከፋ ክፍለ ሀገር
- ፪/ ኢሉባቦር ክፍለ ሀገር
- ፫/ ወለጋ ክፍለ ሀገር
- ፬/ ጋሞ ጐፋ ክፍለ ሀገር

መ) የደቡብ እዝ ፤
- ፩/ ባሌ ክፍለ ሀገር
- ፪/ ሲዳሞ ክፍለ ሀገር

ሠ) የምሥራቅ እዝ ፤
- ፩/ ሐረርጌ ክፍለ ሀገር

፪/ የእዝ አዛዦች በመንግሥት ይሾማሉ ።

፰ ፤ የእዝ አዛዦች ተግባርና ሥልጣን ፤

የእዝ አዛዦች የሚከተሉት ተግባርና ሥልጣን ይኖራቸዋል ፤

፩/ ከብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ በሚሰጠው መመሪያና ትዕዛዝ መሠረት በእዛቸው ውስጥ የሚገኙትን የመደበኛ ጦር ፤ የፖሊስ ሠራዊት እና ሕዝባዊ ሠራዊት በግዳጅ የማሠማራት ፤

፪/ በእዙ ውስጥ ላሉት የክፍላተ ሀገር የአብዮት ዘመቻ ማስተባበሪያ ኮሚቴዎች በዚህ አዋጅ የተጣለባቸውን ኃላፊነት በሚገባ እንዲያከናውኑ የሚያስችላቸውን መመሪያዎች የመስጠት ፤ መመሪያዎቹ በሚገባ በሥራ ላይ መዋላቸውን በቅርብ የመቆጣጠር ፤ የማረጋገጥ ፤ የማስተባበር ፤

፫/ በዕዙ ውስጥ ያሉትን ክፍላተ ሀገር የፀጥታ ሁኔታ እየተከታተለ መደበኛውን ጦር ፤ የፖሊስ ሠራዊቱንና ሕዝባዊ ሠራዊቱን በማስተባበር ፀረ አንድነትና ፀረ አብዮት ኃይሎችን የመደምሰስ ፤

4) to coordinate the financial, moral and other forms of assistance required to support the forces engaged from time to time in the battle-field in defense of the unity of the Country and the Revolution and make continued efforts with a view to increasing said assistance;

5) to agitate and rally the broad masses for the purpose of safeguarding and consolidating the gains of the Ethiopian Revolution and protecting the territorial integrity and independence of the country.

Chapter 3

SECTOR COMMANDS AND THE OPERATIONS COUNCIL

7. *Sector Commands*

1) To repel and crush the invasion and encirclement against the unity of the Country and the Revolution, and to direct in a co-rdinated manner the revolutionary participation of the people, the following five sector commands are hereby established:

a) Central Sector Command:
1. Addis Ababa
2. Shoa Region
3. Arsi Region
4. Wollo Region
5. Gojam Region

b) Northern Sector Command
1. Tigrai Region
2. Eritrea Region
3. Gondar Region

c) Western Sector Command
1. Keffa Region
2. Illubabur Region
3. Wollega Region
4. Gamo Gofa Region

d) Southern Sector Command
1. Bale Region
2. Sidamo Region

e) Eastern Sector Command
Hararghie Region.

2) Sector Commanders shall be appointed by the Government.

8. *Powers and Duties of Sector Commanders*

Sector Commanders shall have the following powers and duties:

1) to deploy the regular army, the police and the militia within their respective sectors in accordance with the directives and orders issued by the National Revolutionary Operations Command;

2) to issue directives to the Regional Revolutionary Operations Co-ordinating Committee in their respective sectors with a view to enabling them to properly implement their duties under this Proclamation and to closely supervise, ensure and co-ordinate the proper implementation of such directives;

3) to follow up the security conditions of the regions in their respective sectors and to liquidate anti-unity and anti-revolution forces by coordinating the regular army, the police and the militia;

ECLN

http://www.ethcriminalawnetwork.com/

፬/ ግዳጃቸውን በጀግንነት ፤ በመሥዋዕትነትና በታላቅ ሥነ ምግባር የፈጸሙትን የመደበኛ ጦር ፤ የፖሊስ ሠራዊትና ሕዝባዊ ሠራዊት አባሎች እየመዘገበ ይህንኑ ለብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ የማስተላለፍ ።

፱፤ የእዝ ቀጠና የዘመቻ ጉባኤ መቋቋም ፤

በያንዳንዱ የዕዝ ቀጠና ውስጥ የእዝ ቀጠና ዘመቻ ጉባኤ ተቋቁሟል ።

፲፤ የእዝ ቀጠና የዘመቻ ጉባኤ አባሎች ፤

የእዝ ቀጠና ዘመቻ ጉባኤ አባሎች የሚከተሉት ይሆናሉ ።

፩/ የእዝ አዛዥ .... ሰብሳቢ
፪/ በእዙ ቀጠና ውስጥ የሚገኝ የያንዳንዱ ክፍለ ሀገር የደርግ አባል .... ምክትል ሰብሳቢ
፫/ በእዙ ቀጠና ውስጥ የሚገኝ የእያንዳንዱ ክፍለ ሀገር አስተዳዳሪ .... አባል
፬/ በእዙ ቀጠና ውስጥ የሚገኙ የእያንዳንዱ ክፍለ ሀገር የጦር አዛዥ . . . . »
፭/ በእዙ ቀጠና ውስጥ የሚገኙ የእያንዳንዱ ክፍለ ሀገር የሕዝባዊ ሠራዊት አዛዥ . . . »
፮/ በእዙ ቀጠና ወ ስጥ የሚገኙ የእያንዳንዱ ክፍለ ሀገር የፖሊስ አዛዥ . . . . . . »
፯/ በእዙ ቀጠና ውስጥ የሚገኙ የእያንዳንዱ ክፍለሀገር የወታደራዊ ፖለቲካ ጉዳይ ካድሬ . . »
፰/ በእዙ ቀጠና ውስጥ የሚገኙ የእያንዳንዱ ክፍለ ሀገር የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ . . . . »
፱/ በእዙ ቀጠና ውስጥ የሚገኙ የእያንዳንዱ ክፍለ ሀገር የገበሬ ማኅበር ተወካይ . . . . »
፲/ በእዙ ቀጠና ውስጥ የሚገኙ የእያንዳንዱ ክፍለ ሀገር የመ.ኢ.ሰ.ማ.ተወካይ . . . »
፲፩/ በእዙ ቀጠና ውስጥ የሚገኙ የእያንዳንዱ ክፍለ ሀገር የወጣቶች ማኅበር ተወካይ . . . »
፲፪/ በእዙ ቀጠና ውስጥ የሚገኙ የእያንዳንዱ ክፍለ ሀገር የሴቶች ማኅበር ተወካይ . . . . »

፲፩፤ የእዝ ቀጠና የዘመቻ ጉባኤ ተግባርና ሥልጣን ፤

የእዝ ቀጠና የዘመቻ ጉባኤ የሚከተሉት ተግባርና ሥል ጣኖች ይኖሩታል ፤

፩/ በየጊዜው ከእዝ አዛዦች የሚሰጠውን መግለጫና መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ ለተወከለበት ክፍልና ሕዝ ባዊ ድርጅት የማሳወቅ ፤ ከእነሱም የሚመነጨውን ሐሳብ ለእዝ አዛዡ የማቅረብ ፤

፪/ በክልሉ ውስጥ በዘመቻው ምክንያት ሊደርሱ የሚ ችሉትን የኢኮኖሚ ፤ የፖለቲካና የማኅበራዊ ጉዳይ ቀውሶች የሚስተካከሉበትን መፍትሔ የመሻት ፤

፫/ ዘመቻው በተሳካ ሁኔታ እንዲራመድና ግቡን እንዲ መታ ለእዝ አዛዡ ሐሳብ የማቅረብ ፤

፬/ ኅብረተሰቡ በዘመቻው ሙሉ በሙሉ የሚሳተፍበትን ዕቅድ የማውጣት፤ ሕዝቡን የመቀስቀስ ፤ የማስተባበር፤

፭/ አብዮቱንና የአገሪቱን አንድነት ለመጠበቅ በየጊዜው በጦር ግንባር ለሚሰለፉ ኃይሎች የሚፈለገውን የገንዘብ፤ የሞራልና የልዩ ልዩ ርዳታዎች ድጋፍ የማስተባበር ፤ ድ ... የማያቋርጥ ጥረት የማድረግ።

4) to register and transmit to the National Revolutionary Operations Command the names of the members of the regular army, the police and the militia who have discharged their duty with great heroism, sacrifice and exemplary discipline.

9. *Establishment of Sector Command Operations Council*

There is hereby established a Sector Command Operations Council within each Sector Command.

10. *Composition of the Sector Command Operations Council*

The Sector Command Operations Council shall have the following members:

1)	The Sector Commander	Chairman
2)	Provisional Military Administration Council representative of each Region within the Sector Command	Vice-Chairman
3)	The Chief Administrator of each Region within the Sector Command	Member
4)	The Commander of the Armed Forces within the Sector Command	"
5)	The Commander of the Militia within the Sector Command	"
6)	The Commissioner of Police of each Region within the Sector Command	"
7)	The Cadre of Military Political Affairs of each Region within the Sector Command. .	"
8)	The Head of the Provisional Office for Mass Organizational Affairs of each Region within the Sector Command	"
9)	A representative of Peasant Associations of each Region within the Sector Command. .	"
10)	A representative of the All-Ethiopia Trade Union of each Region within the Sector Command	"
11)	A representative of the Youth Organization of each Region within the Sector Command.	"
12)	A representative of the Women's Association of each Region within the Sector Command	"

11. *Powers and Duties of the Sector Command Operations Council*

The Sector Command Operations Council shall have the following powers and duties:

1) to transmit reports and directives it receives from the Sector Commander to the respective bodies and mass organizations it represents; and to transmit the suggestions of said bodies and mass organizations to the Sector Commander;
2) to submit proposals on ways of solving the economic, social and political dislocations within its sector arising from its operations;
3) to advise the Sector Commander on ways of making the operation successful and achieve its goals;
4) to prepare plans for the full participation of the people in the operation; and to agitate and rally the people;
5) to coordinate the financial, moral and other forms of assistance required to support the forces engaged from time to time in the battle field in defence of the unity of the Country and the Revolution and to make continues efforts with a view to increasing said assistance.

ECLN

http://www.ethcriminalawnetwork.com/

ምዕራፍ አራት

የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴዎች

፲፪ ፡ የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴዎች ስለመቋቋማቸው

በዚህ ምዕራፍ የተመለከቱት ተግባሮችና ሥልጣኖች ያሏቸው የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴዎች በአዲስ አበባ በአጠቃላይና በከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች ማኅበር በቀሩት ቦታዎች በክፍለ ሀገር ፣ በአውራጃና በወረዳ ደረጃ ተቋቁመዋል ።

፲፫፣ የክፍለ ሀገር የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኰሚቴ አባሎች

የክፍለ ሀገር የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ አባሎች የሚከተሉት ይሆናሉ ፤

፩/ በክፍለ ሀገር የተመደበ የደርግ አባል . . . . ሰብሳቢ

፪/ የክፍለ ሀገር አስተዳዳሪ . . . . . . ምክትል ሰብሳቢ

፫/ በክፍለ ሀገር የሚገኝ ቀደምት የጦር ክፍል አዛዥ..አባል

፬/ የክፍለ ሀገሩ የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ወኪል . . . . አባል

፭/ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተወካይ . . . . . . አባል

፮/ የእርሻና የሕዝብ ማስፈር ሚኒስቴር ተወካይ . . . አባል

፯/ የክፍለ ሀገሩ ፖሊስ ሠራዊት አዛዥ . . አባል

፰/ የክፍለ ሀገሩ የወታደራዊ ፖለቲካ ጉዳይ ካድሬ . . »

፱/ የ. መ. ኢ. ሰ. ማ. ፪ ተወካዮች . . . . »

፲/ የአርበኞች ማኅበር ተወካይ . . . . »

፲፩/ የሴቶች ማኅበር ተወካይ . . . . »

፲፪/ የወጣቶች ማኅበር ተወካይ . . . . »

፲፫/ የክፍለ ሀገሩ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ . . . . »

፲፬/ የገበሬ ማኅበር ተወካይ . . . . »

፲፭/ እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች አግባብ ያላቸው መሥሪያ ቤቶች ወኪሎች . . . . »

፲፬ ፡ የክፍለ ሀገር የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ሥልጣን ፤

የክፍለ ሀገር የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚከተሉት ተግባርና ሥልጣን ይኖሩታል ፤

፩/ ከእዝ አዛዡ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ወዝ አደሩ ፣ ገበሬው ፣ የከተማ ነዋሪዎች ፣ አርበኞች ፣ እንደዚሁም የሴቶችና የወጣቶች ማኅበራት በዘመቻው እንዲሣተፉ የማስተባበር ፣ የማንቃት ፣ የማደራጀት ፤

፪/ ግንባር ቀደም የሚሆኑት ዘማቾች እንዲመዘገቡ ፣ እንዲመለመሉ ፣ እንዲሰለጥኑ ፣ የማስተባበርና የመቆጣጠር ፤

፫/ የደጀን ተዋጊ ዘማች ሠራዊት እንዲመለመሉ ፣ እንዲሰለጥኑ መመሪያ የመስጠት ፤

፬/ የአውራጃ የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ መሠረት የሚያከናውኑትን ተግባር የማስተባበር ፣ የመቆጣጠር ፤

፭/ ተግባሩን ከግቡ ለማድረስ ንዑስ አካሎችን የማቋቋም ፣ መመሪያዎችን የመስጠት ፤

፮/ ከሕዝብ የሚገኘውን እርዳታ የመቀበል ፣ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት መቀመጡንና ወደሚፈለገው አድራሻ መድረሱን የማረጋገጥ ፤

፯/ በየአውራጃው ያሉትን ፀረ አብዮትና ፀረ አንድነት ተግባሮች እየተከታተለ በየአውራጃው ያሉት የአብዮት የዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴዎች ሁኔታውን እንዲያውቁትና አስፈላጊዎቹን እርምጃዎች እንዲወስዱ የማድረግ፤

Chapter Four

REVOLUTIONARY OPERATIONS COORDINATING COMMITTEES

12. *Establishment of Revolutionary Operations Coordinating Committees*

There are hereby established Revolutionary Operations Coordinating Committees charged with powers and duties specified in this chapter in Addis Ababa, at the Central and Higher Urban Dwellers Association levels; and at the Regional, Awardja and Woreda levels elsewhere in the Country.

13. *Composition of the Regional Revolutionary Operations Coordinating Committee*

The Regional Operations Coordinating Committee shall have the following members:

1) A representative of the Provisional Military Administration Council of the Region . . . . Chairman
2) The Chief Administrator of the Region . . . . Vice-Chairman
3) The Senior Commander of the Armed Forces in the Region . . . . Member
4) A representative of the Ministry of Transport and Communications of the Region . . "
5) A representative of the Ministry of Health "
6) A representative of the Ministry of Agriculture and Settlement . . . . "
7) The Commissioner of Police of the Region . . . . "
8) The military Political Cadre of the Region . . . . "
9) Two representatives of the All-Ethiopia Trade Union . . . . "
10) A representative of the Patriots' Association . . . . "
11) A representative of Women's Association "
12) A representative of Youth Organization . . "
13) The head of the Provisional Office for Mass Organizational Affairs of the Region "
14) A representative of Peasant Association . . "
15) Representatives of other appropriate government offices as may be necessary . . Members

14. *Powers and Duties of the Regional Revolutionary Operations Coordinating Committee*

The Regional Revolutionary Operations Coordinating Committee shall have the following powers and duties:

1) to coordinate, politicize, and organize workers, peasants, urban dwellers, patriots, women and youth organizations to participate in the operations in accordance with directives to be issued by the Sector Commander;
2) to coordinate and supervise the registration, conscription and training of vanguard forces;
3) to issue directives for the registration, conscription and training of rear guards;
4) to coordinate and supervise the activities of the Awradja Revolutionary Operations Coordinating Committees under Article 16 hereof;
5) to establish and issue directives to sub-organs to achieve its objectives;
6) to receive aid extended by the people and, in accordance with directives issued to it ensure that it is deposited and reaches its proper destination;
7) to follow up anti-revolutionary and anti-unity activities in every Awradja and inform Awradja Revolutionary Operations Coordinating Committees of the situation and cause them take appropriate action;

ECLN

http://www.ethcriminalawnetwork.com/

፰/ በክፍለ ሀገሩ ውስጥ አጠቃላይ የፀረ አብዮትና የፀረ አንድነት ኃይሎች አሰሳ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ በየአውራጃው ያሉትን የሰፊውን ሕዝብ ወገን በማስተባበር አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ ፤

፱/ በክፍለ ሀገሩ ውስጥ ፀረ አብዮትና ፀረ አንድነት ፀረ ዘመቻ ተግባር በሚፈጽምና ወይም መሬት እንዳይታረስ ፤ ምርት እንዳይዳብር ፤ ምርት ወደገበያ እንዳይወጣ እና ሌሎችንም ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ አሻጥር የሚፈጽም ለመሆኑ የሚጠረጠረውን ማንኛውንም ሰው እስከ ስድስት ወር ድረስ በማረፊያ ቤት እንዲቆይ የማድረግ ፤ በነዚሁ ወንጀሎች የሚያስከስስ ማስረጃ ሲገኝበት ሥልጣን ወደአለው ፍርድ ቤት እንዲቀርብ የማድረግ ፤

፲/ በፕላኑ መሠረት ከልዩ ልዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚላከውን የልማት ፕሮግራም እና በሕዝብ መዋጮ የሚካሄዱትን የልማት ሥራዎች በሥራ ላይ በወቅቱ መዋላቸውን የመቆጣጠር ፤ የማስተዳደር ፤

፲፩/ በመጀመሪያ ደረጃ በአውራጃ የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የሚቀርቡትን ኀቤቱታዎች መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት ፤

፲፪/ የራሱን የውስጥ ደንብ የማውጣት ፡፡

፲፭ ፡ የአውራጃ የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ አባሎች

የአውራጃ የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ አባሎች የሚከተሉት ይሆናሉ ፡

፩/ የአውራጃ አስተዳዳሪ . . . . ሰብሳቢ
፪/ የአውራጃው የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ . . . . ምትክል ሰብሳቢ
፫/ የአውራጃው ፖሊስ አዛዥ . . . . አባል
፬/ በአውራጃው የሚገኝ የጦር ክፍል አዛዥ . . . . አባል
፭/ የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ወኪል . . አባል
፮/ የእርሻና የሕዝብ ማስፈር ሚኒስቴር ወኪል . . . »
፯/ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ወኪል . . . . »
፰/ የአውራጃው የገበሬ ማኅበር ፪ ተወካዮች . . . . አባል
፱/ የአውራጃው የከተማ ነዋሪዎች ማኅበራት ፪ ተወካዮች . . . . አባል
፲/ የአውራጃው የወጣቶች ተወካይ . . . . »
፲፩/ የአውራጃ የሴቶች ማኅበር ተወካይ . . . . . . አባል
፲፪/ የአውራጃው የመ. ኢ. ሠ. ማ. ፪ ተወካዮች አባል
፲፫/ እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች አግባብ ያላቸው መሥሪያ ቤቶች ወኪሎች . . . . አባል

፲፮ ፡ የአውራጃ የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ሥልጣን ፤

የአውራጃው የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚከተሉት ተግባርና ሥልጣን ይኖሩታል ፤

፩/ ከየወረዳው የሚመለመሉት ግንባር ቀደም ዘማቾች ለውጊያ መዘጋጀታቸውን የማረጋገጥ ፤ እንደአስፈላጊነቱም ከክፍለ ሀገር የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ የዘመቻ ትእዛዝ መሠረት የማዝመት ፤

፪/ በውስጡ ያሉት የወረዳ የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፰ መሠረት የሚያከናውኑትን ተግባር የማስተባበር ፤ የመቈጣጠር ፤

፫/ በአውራጃው ለዘመቻ ድጋፍ ሊሰጡ የሚችሉ ዝግጅቶች መሟላታቸውን የማረጋገጥ ፤

8) to mobilize the allies of the broad masses in every Awradja and take the necessary measures when an overall search campaign against anti-revolutionary and anti-unity forces in the Region becomes necessary;

9) to put under detention for a period not exceeding six anti-unity forces in the Region becomes necessary anti-unity or anti-operations acts or who is suspected of having committed acts of sabotage against the tilling of land, the increase of production, the marketing of produce or various other acts of economic sabotage, and upon sufficient evidence that he has committed such offences, take measures that such person is prosecuted before a competent court;

10) to supervise and administer the implementation of development programmes sent from Government offices to be carried out jointly by public contributions in accordance with the plan;

11) to examine and give final decision on matters decided on first instance by the Awradja Revolutionary Operations Coordinating Committee;

12) to issue its internal regulations.

15. *Composition of the Awradja Revolutionary Operations Coordinating Committee*

The Awradja Revolutionary Operations Coordinating Committee shall have the following members:

1) The Awradja Administrator . . . . Chairman
2) The head of the Awradja Provisional Office for Mass Organizational Affairs . . . . Vice-Chairman
3) The Awradja Police Chief . . . . Member
4) The Commander of the Military Unit stationed within the Awradja . . . . ,,
5) A representative of the Ministry of Transport and Communications . . . . ,,
6) A representative of the Ministry of Agriculture and Settlement . . . . ,,
7) A representative of the Ministry of Health . . . . ,,
8) Two representatives of the Awradja Peasant Association . . . . ,,
9) Two representatives of the Awradja Urban Dwellers' Associations . . . . ,,
10) A representative of the Awradja Youth Organization . . . . ,,
11) A representative of the Awradja Women's Association . . . . ,,
12) Two representatives of the All-Ethiopia Trade Union of the Awradja . . . . ,,
13) Representatives of other appropriate government offices as may be necessary . . ,,

16. *Powers and Duties of the Awradja Revolutionary Operations Coordinating Committee*

The Awradja Revolutionary Operations Coordinating Committee shall have the following powers and duties:

1) to ensure that the vanguard participants conscripted from every Woreda are prepared for combat and to deploy them in accordance with the orders for deployment of the Regional Revoltuionary Operations Coordinating Committee as may be necessary;

2) to coordinate and supervise the activities of the Woreda Revolutionary Operations Cordinating Committees under Article 18 hereof;

3) to ensure that all resources which can give support to the operation are mobilized;

ECLN

http://www.ethcriminalawnetwork.com/

፬/ ከሕዝቡ የሚገኘውን እርዳታ የመቀበል ፤ በሚሰጠውም መመሪያ መሠረት መቀመጡንና ወደሚፈለገው አድራሻ መድረሱን ማረጋገጥ ፤

፭/ በአውራጃው ውስጥ አጠቃላይ የፀረ አብዮትና የፀረ አንድነት ኃይሎች አሰሳ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ በየወረዳው ያሉትን የሰፊውን ሕዝብ ወገን በማስተባበር እንደሁኔታው ተገቢውን እርምጃ የመውሰድ ፤

፮/ በየወረዳው ያሉትን የፀረ አብዮትና የፀረ አንድነት ተግባሮች እየተከታተሉ በየወረዳው ያሉት አግባብ ያለው የወረዳ የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ ሁኔታውን እንዲያውቀውና አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስድ የማድረግ ፤

፯/ በአውራጃው ውስጥ ፀረ አብዮትና ፀረ አንድነት ፀረ ዘመቻ ተግባር በሚፈጽምና ወይም መሬት እንዳይታረስ ፤ ምርት እንዳይዳብር ፤ ምርት ወደገበያ እንዳይወጣ እና ሌሎችንም ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ አሻጥር የሚፈጽም ለመሆኑ የሚጠረጠረውን ማንኛውንም ሰው እስከ ስድስት ወር ድረስ በማረፊያ ቤት እንዲቆይ የማድረግ ፤ በነዚህ ወንጀሎች የሚያስከስስ ማስረጃ ሲገኝበትም ሥልጣን ወደአለው ፍርድ ቤት እንዲቀርብ የማድረግ ፤

፰/ በአውራጃ ደረጃ የሚካሄዱትን የልማት ሥራዎች በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የማስተባበር ፤

፱/ በወረዳው የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርብለትን አቤቱታ መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት ፤

፲/ ተግባሩን ከግቡ ለማድረስ ንዑስ አካሎችን የማቋቋምና መመሪያዎችን የማውጣት ፤

፲፩ የራሱን የውስጥ ደንብ የማውጣት ።

፲፯/ የወረዳ የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ አባሎች

የወረዳ የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ አባሎች የሚከተሉት ይሆናሉ ፤

፩/ የወረዳው አስተዳዳሪ .. .. ሰብሳቢ
፪/ የወረዳው የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ .... ምክትል ሰብሳቢ
፫/ በወረዳው ክልል ውስጥ የሚገኝ የጦር አዛዥ አባል
፬/ የወረዳው ፖሊስ አዛዥ.... .... »
፭/ የእርሻና የሕዝብ ማስፈር ሚኒስቴር ተወካይ .... »
፮/ የሕዝብ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተወካይ .... »
፯/ የወረዳው የገበሬ ማኅበር ፫ ተወካዮች ... . »
፰/ የወረዳው የሴቶች ማኅበር ተወካይ .... »
፱/ በወረዳው ክልል ውስጥ የሚገኙ የከተማ ነዋሪዎች ማኅበራት ፪ ተወካዮች .... »
፲/ የመ. ኢ. ሰ. ማ. ፪ ተወካዮች....... ... »
፲፩/ የወረዳው የወጣቶች ማኅበር ተወካይ ....»
፲፪/ ሌሎች አግባብ ያላቸው መሥሪያ ቤቶች ወኪሎች »

፲፰/ የወረዳ የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ሥልጣን

የወረዳ የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚከተሉት ተግባርና ሥልጣን ይኖሩታል ፤

4) to receive aid extended by the people and in accordance with directives issued to it, ensure that it is deposited and reaches its proper destination;

5) to mobilize the allies of the broad masses from every Woreda and take the necessary measures when an overall search campaign against anti-revolutionary and anti-unity forces in the Awradja becomes necessary;

6) to follow up anti-revolutionary and anti-unity activities in every Woreda and inform the concerned Woreda Revolutionary Operations Coordinating Committees of the situation and cause them take appropriate action;

7) to put under detention for a period of not exceeding six months any person who commits anti-revolutionary, anti-unity or anti-operations acts or who is suspected of having committed acts of sabotage against the tilling of land, the increase of production, the marketing of produce or various other acts of economic sabotage, and, upon sufficient evidence that he has committed such offences, take measures that such person is prosecuted before a competent court;

8) in accordance with directives to be given to it, to coordinate development programmes carried on at the Awradja level;

9) to examine and give final decision on complaints against the decisions of the Woreda Revolutionary Operations Coordinating Committee;

10) to establish and issue directives to sub-organs to achieve its objectives;

11) to issue its internal regulations.

17. *Composition of the Woreda Revolutionary Operations Coordinating Committee*

The Woreda Revolutionary Operations Coordinating Committee shall have the following members:

1) The Woreda Administrator .. .. Chairman
2) Head of the Woreda Branch of the Provisional Office for Mass Organizational Affairs .... Vice-Chairman
3) The Commander of the Military Unit stationed within the Woreda .. .. Member
4) The Woreda Police Chief .... "
5) A representative of the Ministry of Agriculture and Settlement .. .. "
6) A representative of the Ministry of Health .... "
7) Three representatives of the Woreda Peasant Association .... "
8) A representative of the Woreda Women's Association. .... "
9) Two representatives from Urban Dwellers' Associations within the Woreda .... "
10) Two representatives of the All-Ethiopia Trade Union .... "
11) A representative of the Woreda Youth Organization .... "
12) Representatives of other appropriate Government offices .... "

18. *Powers and Duties of the Woreda Revolutionary Operations Coordinating Committee*

The Woreda Revolutionary Operations Coordinating Committee shall have the following powers and duties:

http://www.ethcriminalawnetwork.com/

፩/ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የግንባር ቀደምና የደጀን ተዋጊ ዘማቾችን የመመዝገብ ፣ የመመልመልና ወታደራዊና የፖለቲካ ትምህርት የመስጠት ፣ የአካባቢውን ሕዝብ ለዘማች ሠራዊቱ ስንቅ ፣ ትጥቅና መጓጓዣ በማዘጋጀትና በማቅረብ ፣ ዘማች ሠራዊቱን በሕክምና በመርዳትና ቤተሰቡንና ንብረቱን በመንከባከብ ፣ አብዮቱን በመጠበቅ የሚያደርገውን ተሳትፎ የማስተባበር ፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከቱትን ተግባሮች በሚገባ በሥራ ላይ ለማዋል ፣ የዘማች ሠራዊት ምልመላና ምዝገባ ፣ የወታደራዊና የፖለቲካ ትምህርት ፣ የስንቅ ፣ የትጥቅ ፣ የመጓጓዣ ፣ የዘማች ሠራዊት ቤተሰብና ንብረት እንክብካቤ ፣ የአብዮት ጥበቃና ሌሎችም አስፈላጊ የሆኑ ኮሚቴዎችን ፣ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የማቋቋም ፣ ተግባራቸውን የማቀነባበር ፣ የመምራትና የመቆጣጠር ፤

፫/ የዘመቻውን ዕቅድ የማውጣት ፣ የሚዘምተውን ሕዝባዊ ሠራዊት የመደልደልና አዝማች የመመደብ ፤

፬/ ከአውራጃው የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚመጣለትን ትእዛዝ የመፈጸም ፤

፭/ ዘመቻ በሚደረግበት አካባቢ ከጠላት ተጽዕኖ ነፃ የሚወጣውን ሕዝብ አደራጅቶና አስታጥቆ ለውጊያ እንዲሰለፍ የማድረግ ፤

፮/ ከሕዝብ የሚገኘውን ርዳታ የመቀበል ፤ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት መቀመጡንና ወደሚፈለገው አድራሻ መድረሱን የማረጋገጥ ፤

፯/ በዘመቻውና ፀረ አብዮትና ፀረ አንድነት ኃይሎችን ለመደምሰስ በሚደረገው አሰሳ ሕዝቡ ተካፋይ እንዲሆን ሕዝቡን የመቀስቀስ ፣ የማስተባበርና የማሰማራት ፤

፰/ ሕዝቡ ከጠላት ፣ ከጥቃት እራሱን የሚከላከልበትን ዘዴ የማስተባበር ፤

፱/ ፀረ አብዮትና ፀረ አንድነት ፀረ ዘመቻ ተግባር በሚፈጽም ወይም መሬት እንዳይታረስ ምርት እንዳይዳብር ፣ ምርት ወደገበያ እንዳይወጣ እና ሌሎችንም ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ አሻጥር የሚፈጽም ለመሆኑ የሚጠረጠረውን ማንኛውንም ሰው እስከ ሦስት ወር ድረስ በማረፊያ ቤት እንዲቆይ የማድረግ ፣ በነዚሁ ወንጀሎች የሚያስከስስ ማስረጃ ሲገኝበትም ሥልጣን ወደአለው ፍርድ ቤት እንዲቀርብ የማድረግ ፤

፲/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ሕዝባዊ ድርጅቶችን በነርሱም ሥር የሚቋቋሙትን ማኅበሮች ሥራ የማስተባበርና የመቆጣጠር ፤

፲፩/ የመገናኛ መሥመሮችን ድልድዮችንና ልዩ ልዩ የመንግሥት የሕዝብ ንብረቶችን እንዲጠበቁ የማስተባበርና የመቆጣጠር ፤

፲፪/ በፕላኑ መሠረት ከአውራጃው የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚላከውን የልማት ፕሮግራም በሥራ ላይ መዋሉን የመቆጣጠር ፣ የማስተባበር ፤

፲፫/ የራሱን የውስጥ ደንብ የማውጣት ።

፲፱። የአዲስ አበባ አጠቃላይ የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ አባሎች ፤

የአዲስ አበባ አጠቃላይ የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚከተሉት አባሎች ይኖሩታል ፤

1) in accordance with directives to be issued to it, to register, conscript and give military and political training to vanguard and rearguard forces; to coordinate the activities of the people in the preparation and supply of logistics, medical aid, in caring for the family of participants, their property and in safeguarding the Revolution;

2) for the purpose of implementing properly the activities referred to in sub-article 1 of this Article, to establish, coordinate the activities of, guide and supervise conscription and registration, military and political education, logistics, participants' family and property care, revolutionary defense and other committees in accordance with directives to be issued to it;

3) to plan the operation, assign the militia and leaders therefor;

4) to execute orders sent to it from the Awradja Revolutionary Operations Coordinating Committee;

5) to organize, arm and prepare for fighting people liberated from the influence of the enemy;

6) to receive aid extended by the people and in accordance with directives issued to it ensure that it is deposited and reaches its proper destination;

7) to agitate and co-ordinate the people to participate and assign them in the Operations and in the search campaign to liquidate anti-revolution and anti-unity elements;

8) to coordinate the activities of the people in defending themselves from the enemy and aggression;

9) to put under detention for a period not exceeding three months any person who commits anti-revolutionary, anti-unity or anti-operations acts or who is suspected of having committed acts of sabotage against the tilling of land, the increase of production, the marketing of produce or various other acts of economic sabotage, and upon sufficient evidence that he has committed such offences, take measures that such person is prosecuted before a competent court;

10) to coordinate and supervise the activities of government offices and mass organizations and associations formed under the latter;

11) to coordinate and supervise the activities of the people in protecting communication lines, bridges and government and public property;

12) to supervise and coordinate the implementation of development programs sent to it from the Awradja Revolutionary Operations Coordinating Committee in accordance with the plan;

13) to issue its internal regulations.

19. *Composition of the Addis Ababa Central Revolutionary Operations Coordinating Committee*

The Addis Ababa Central Revolutionary Operations Coordinating Committee shall have the following members:

ECLN

http://www.ethcriminalawnetwork.com/

፩/ የደርግ አባል . . . . ሰብሳቢ
፪/ የከተማው ከንቲባ . . . . ምክትል ሰብሳቢ
፫/ ከአጠቃላይ ማኅበር ቋሚ ኮሚቴ ፩ ተወካይ . . አባል
፬/ የአገር አስተዳደር ሚኒስቴር ተወካይ . . . . »
፭/ የሠራተኛና የማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ተወካይ »
፮/ የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር ተወካይ . . . . . »
፯/ የአዲስ አበባ ፖሊስ አዛዥ . . . . »
፰/ የአዲስ አበባ ከተማ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ . . . . አባል
፱/ የመላ ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ተወካይ. . . . »
፲/ የ፩ኛ ክፍለ ጦር ተወካይ . . . . »
፲፩/ የአጠቃላይ የሴቶች ማኅበር ተወካይ . . . . »
፲፪/ የአጠቃላይ የወጣቶች ማኅበር ተወካይ . . . . »

፳፣ የአዲስ አበባ አጠቃላይ የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ሥልጣን ፣

የአዲስ አበባ አጠቃላይ ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚከተሉት ተግባርና ሥልጣን ይኖሩታል ፣

፩/ ከእዝ አዛዥ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ወዝ አደሩ ፣ የከተማ ነዋሪዎች ፣ አርበኞች ፣ የሴቶችና የወጣቶች ማኅበራት በዘመቻው እንዲሣተፉ የማስተባበር ፣ የማንቃት ፣ የማደራጀት ፣

፪/ በአዲስ አበባ የሚገኙትን ግንባር ቀደም የሚሆኑትን ዘማቾችን እንዲመዘገቡ ፣ እንዲመለመሉ ፣ እንዲሰለጥኑ ፣ የማስተባበር ፣ የመቆጣጠር

፫/ የደጀን ተዋጊ ዘማች ሠራዊት እንዲመዘገብ ፣ እንዲመለመል ፣ እንዲሰለጥን መመሪያ የመስጠት ፣

፬/ በውስጡ ያሉት የከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪ መሠረት የሚያከናውኑትን ተግባር የማስተባበር ፣ የመቆጣጠር ፣

፭/ ተግባሩን ከግቡ ለማድረስ ንኡስ አካሎችን የማቋቋምና መመሪያዎችን የመስጠት ፣

፮/ ከሕዝቡ የሚገኘውን እርዳታ የመቀበል ፣ በሚሰጠውም መመሪያ መሠረት መቀመጡንና ወደሚፈለገው አድራሻ መድረሱን ማረጋገጥ ፣

፯/ በከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች ማኅበር የአስተዳደር ክልል ውስጥ ያሉትን ፀረ አብዮትና ፀረ አንድነት ተግባሮች እየተከታተለ የሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና በውስጡ ያሉት የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴዎች ሁኔታውን እንዲያውቁት እና እንዲከታተሉት የማድረግ ፣

፰/ በአዲስ አበባ ክልል ውስጥ ፀረ አብዮትና ፀረ አንድነት ጸረ ዘመቻ ተግባር በሚፈጸምና ምርት እንዳይዳብር ፣ ምርት ወደገበያ እንዳይወጣ እና ሌሎችንም ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ አሻጥር የሚፈጽም ለመሆኑ የሚጠረጠረውን ማንኛውንም ሰው እስከ ስድስት ወር ድረስ በማረፊያ ቤት እንዲቆይ የማድረግ ፣ በነዚሁ ወንጀሎች የሚያስከስስ ማስረጃ ሲገኝበትም ሥልጣን ወደአለው ፍርድ ቤት እንዲቀርብ የማድረግ ፣

፱/ በመጀመሪያ ደረጃ በከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የሚቀርቡትን አቤቱታዎች መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት ፣

1) A member of the Provisional Military Administration Council . . . . Chairman
2) The Mayor of the City . . . . Vice-Chairman
3) A representative of the Standing Committee of the Central Urban Dwellers' Association Member
4) A representative of the Ministry of Interior »
5) A representative of the Ministry of Labour and Social Affairs . . . . »
6) A representative of the Ministry of Urban Development and Housing . . . . »
7) Commissioner of Police of Addis Ababa . . »
8) Head of the Provisional Office for Mass Organizational Affairs of Addis Ababa . . . »
9) A representative of the All-Ethiopia Trade Union . . . . »
10) A representative of the First Army Division »
11) A representative of the Central Women's Association. . . . . »
12) A representative of the Central Youth Organization . . . . »

20. *Powers and Duties of the Addis Ababa Central Revolutionary Operations Coordinating Committee*

The Addis Ababa Central Revolutionary Operations Coordinating Committee shall have the following powers and duties:

1) to coordinate, politicize, and organize workers, peasants, urban dwellers, patriots, women and youth organizations to participate in the operations in accordance with directives to be issued by the Sector Commander;
2) to coordinate and supervise the registration, conscription and training of vanguard forces from Addis Ababa;
3) to issue directives for the registration, conscription and training of rear guards;
4) to coordinate and supervise the activities of the Higher Urban Dwellers' Association Revolutionary Operations Coordinating Committees under Article 22 hereof;
5) to establish and issue directives to sub-organs to achieve its objectives;
6) to receive aid extended by the people and, in accordance with the directives issued to it, ensure that it is deposited and reaches its proper destination;
7) to follow up anti-revolutionary and anti-unity activities in every Higher Urban Dwellers' Association and inform the concerned Government offices and Revolutionary Operations Coordinating Committees under it of the situation and cause them take appropriate action;
8) to put under detention for a period not exceeding six months any person who commits anti-revolutionary, anti-unity or anti-operations acts or who is suspected of having committed acts of sabotage against the increase of production, the marketing of produce or various other acts of economic sabotage in Addis Ababa and upon sufficient evidence that he has committed such offences, take measures that such person is prosecuted before a competent court;
9) to give final decision on matters decided on first instance by the Higher Urban Dwellers' Association Revolutionary Operations Coordinating Committee;

ECLN

http://www.ethcriminalawnetwork.com/

፲/ የራሱን የውስጥ ደንብ የማውጣት ።

፳፩፣ የአዲስ አበባ ከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች የአብዮት ዘመቻ ማስተባበሪያ ኮሚቴ አባሎች ፤

የአዲስ አበባ የከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች የአብዮት ዘመቻ ማስተባበሪያ ኮሚቴ የሚከተሉት አባሎች ይኖሩታል ፤

፩/ የከፍተኛ ማኅበር ሊቀ መንበር.......... ሰብሳቢ
፪/ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት ተወካይ .... ምክትል ሰብሳቢ
፫/ ከከፍተኛ ማኅበር አንድ ተወካይ . . . . አባል
፬/ የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር ተወካይ .... አባል
፭/ የአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ተወካይ .... »
፮/ በከፍተኛ ማኅበር ከሚገኙ የመላ ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር አባል ማኅበራት ሁለት ተወካዮች»
፯/ የከፍተኛ የሴቶች ማኅበር አንድ ተወካይ ....»
፰/ የከፍተኛ የወጣቶች ማኅበር አንድ ተወካይ.....»

፳፪፣ የከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር ፤

የከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል ፤

፩/ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የግምባር ቀደምትና የደጀን ተዋጊ ዘማቾችን የመመዝገብ ፤ የመመልመልና የወታደራዊና የፖለቲካ ትምህርት የመስጠት ፤ የአካባቢውን ሕዝብ ለዘማች ሠራዊቱ ሥንቅ ትጥቅና መጓጓዣ በማዘጋጀትና በማቅረብ ፤ ዘማች ሠራዊቱን በሕክምና በመርዳትና ቤተሰቡንና ንብረቱን በመንከባከብ ፤ አብዮቱን በመጠበቅ የሚያደርገውን ተሳትፎ የማስተባበር ፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከቱትን ተግባሮች በሚገባ በሥራ ላይ ለማዋል ፤ የዘማች ሠራዊት ምልመላና ምዝገባ ፤ የወታደራዊና የፖለቲካ ትምህርት ፤ የሥንቅ ፤ የትጥቅ ፤ የመጓጓዣ ፤ የዘማች ሠራዊት ቤተሰብና ንብረት እንክብካቤ ፤ የአብዮት ጥበቃና ሌሎችም አስፈላጊ የሆኑ ኮሚቴዎችን በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የሚቋቋም ፤ ተግባራቸውን የማቀነባበር ፤ የመምራትና የመቆጣጠር ፤

፫/ ከአጠቃላይ የከተማ ነዋሪዎች የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚመጣለትን ትእዛዝ የመፈጸም ፤

፬/ በክልሉ ውስጥ ለዘመቻ ድጋፍ ሊሰጥ የሚያስችሉ ዝግጅቶች መሟላታቸውን የማረጋገጥ ፤

፭/ ከየቀበሌው የሚመለመሉትን ግንባር ቀደም ዘማቾች ለውጊያ መዘጋጀታቸውን የማረጋገጥ ፤

፮/ ከሕዝብ የሚገኘውን እርዳታ የመቀበል ፤ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት መቀመጡንና ወደሚፈለገው አድራሻ መድረሱን የማረጋገጥ ፤

፯/ በክልሉ ውስጥ ፀረ አብዮትና ፀረ አንድነት ፀረ ዘመቻ ተግባር በሚፈጽምና ምርት እንዳይዳብር ምርት ወደገበያ እንዳይወጣ እና ሌሎችንም ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ አሻጥር የሚፈጽም ለመሆኑ የሚጠረጠረውን ማንኛውንም ሰው እስከ ፫ ወር ድረስ በማረፊያ ቤት እንዲቆይ የማድረግ ፤ በነዚህ ወንጀሎች የሚያስከስስ ማስረጃ ሲገኝበትም ሥልጣን ወዳለው ፍርድ ቤት እንዲቀርብ የማድረግ ፤

10) to issue its internal regulations.

21. *Composition of the Higher Urban Dwellers' Association Revolutionary Operations Coordinating Committee*

The Higher Urban Dwellers' Association Revolutionary Operations Coordinating Committee shall have the following members:

1) The Chairman of the Higher Urban Dwellers' Association . . . . Chairman
2) A representative of the Provisional Office for Mass Organizational Affairs . . . . Vice-Chairman
3) A representative of the Higher Urban Dwellers' Association. . . . . Member
4) A representative of the Ministry of Urban Development and Housing . . . . "
5) A representative of the Addis Ababa Police. . . . . "
6) Two representatives of Workers' Unions within the Higher Urban Dwellers' Association which are members of the All-Ethiopia Trade Union . . . . "
7) A representative of the Higher Women's Association. . . . . "
8) A representative of the Higher Youth Organization . . . . "

22. *Powers and Duties of the Higher Urban Dwellers' Association Revolutionary Operations Coordinating Committee*

The Higher Urban Dwellers' Association Revolutionary Operations Coordinating Committee shall have the following powers and duties:

1) in accordance with directives to be issued to it, to register, conscript and give military and political training to vanguard and rearguard forces; to coordinate the activities of the people in the preparation and supply of logistics, medical aid in caring for the family of participants, their property and in safeguarding the Revolution;
2) for the purpose of implementing properly the activities referred to in Sub-Article 1 of this Article, to establish, coordinate the activities of, guide and supervise conscription and registration, military and political education, logistics, participants' family and property care, revolutionary defense and other committees in accordance with directives to be issued to it;
3) to execute orders sent to it from the Higher Urban Dwellers Revolutionary Operations Coordinating Committee;
4) to ensure that all resources which can give support to the operation are mobilized;
5) to ensure that the vanguard participants conscripted from every Kebele are prepared for combat.
6) to receive aid extended by the people and in accordance with the directives issued to it, ensure that it is deposited and reaches its proper destination;
7) to put under detention for a period not exceeding three (3) months any person who commits anti-revolutionary, anti-unity or anti-operations acts or who is suspected of having committed acts of sabotage against the increase of production, the marketing of produce or various other acts of economic sabotage, and, upon sufficient evidence that he has committed such offences, take measures to prosecute such person before a competent court;

ECLN

http://www.ethcriminalawnetwork.com/

፰/ ከየቀበሌዎቹ የሚደርሱትን የጸረ አብዮትና የጸረ አንድነት መረጃና ሪፖርት አጠናቅሮ ለአጠቃላይ የከተማ ነዋሪዎች የዘመቻ ማስተባበሪያ ኮሚቴ የመላክ፤

፱/ የመገናኛ መሥመሮችን ድልድዮችንና ልዩ ልዩ የመንግሥት የሕዝብ ድርጅቶችና ንብረቶች እንዲጠበቁ የማስተባበር የመቆጣጠር ፤

፲/ የራሱን የውስጥ ደንብ የማውጣት ።

ምዕራፍ አምስት
ልዩ ሥልጣን

፳፫ ፤ የብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ ልዩ ሥልጣን ፤

፩/ የመንግሥት የልማት ፕሮጀክቶችና የዓለም አቀፍ ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ፤ የብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ የአገሪቷን አንድነትና ዳር ድንበር፤ እንደዚሁም በመካሄድ ላይ ያለውን አብዮት ለመጠበቅ፤

ሀ/ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ አስፈላጊ በሆነ ሥራ ላይ እንዲሳተፍ ለማድረግ ፤

ለ/ የመንግሥት ፤ የሕዝባዊ ድርጅቶች ወይም የማናቸውም አካል ወይም ሰው በሆኑ በማናቸውም የትራንስፖርትና መገናኛ አገልግሎት መሣሪያዎች ለመጠቀም፤

ሐ/ የመንግሥት ፤ የሕዝባዊ ድርጅቶች ወይም የማናቸውም አካል ወይም ሰው በሆኑ ማናቸውም መጋዘኖች ፤ ሕንፃዎች ጋራዦች ፤ ፋብሪካዎች ፤ መሣሪያዎች ወይም በማናቸውም መገልገያዎች ለመጠቀም፤

መ/ ለዘመቻው የሚያስፈልጉትን ዕቃዎችና ሸቀጦች እንዲሸጡለት ለማድረግ ፤

ሠ/ አስፈላጊ የሆኑትን ማናቸውንም የንግድ ዕቃዎችን የማምረት ፤ የማከፋፈልና የመሸጥ መብት ሁኔታን ለመቆጣጠር ፤

ይችላል ።

፪/ የብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከቱትን ሥልጣኖች ለእዝ አዛዦች በውክልና ሊሰጥ ይችላል ።

፳፬ ፤ የመተባበር ግዴታ ፤

፩/ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የመንግሥት መሥሪያ ቤት፤ የግል ድርጅት ወይም ሕዝባዊ ድርጅት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚደረገው ዘመቻ የመካፈልና የመተባበር ግዴታ አለበት ፤

፪/ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ፤ የመንግሥት መሥሪያ ቤት፤ የግል ድርጅት ወይም ሕዝባዊ ድርጅት ብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ ፤ የእዝ አዛዡ ወይም የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚሰጠውን ትእዛዝ በቅድሚያ የመፈጸም ግዴታ አለበት ።

፳፭ ፤ ቅ ጣ ት ፤

፩/ ማንኛውም በዚህ አዋጅ መሠረት በወጡ ትእዛዞች ወይም ደንቦች መሠረት ፤

ሀ. የተጣለበትን ግዴታ ያልፈጸመ ፤ ወይም በማናቸውም መንገድ ከግዴታው ለማምለጥ የሞከረ ፤ ወይም ከግዴታው ያመለጠ ፤ ወይም

ለ. ግዴታ የተጣለበት ሰው ግዴታውን እንዳይፈጽም ያነሳሳ ፤ ያበረታታ ፤ ወይም በማናቸውም መንገድ የረዳ ፤ ሰው ፤

እስከ አምስት (፭) ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እሥራት ወይም የነገሩ ሁኔታ እጅግ ከባድ በሚሆንበት ጊዜ እስከ ዕድሜ ልክ ሊደርስ በሚችል ጽኑ እሥራት ወይም በሞት ይቀጣል ።

8) to compile and transmit to the Central Urban Dwellers' Association Revolutionary Operations Coordinating Committee information and report it receives from *Kebeles* concerning anti-revolutionary and anti-unity activities;

9) to coordinate and supervise the activities of the people in protecting communication lines, bridges and government and public property;

10) to issue its internal regulations.

Chapter Five
SPECIAL POWERS

23. *Special Powers of the National Revolutionary Operations Command*

1) Without affecting government development projects and international obligations, the National Revolutionary Operations Command may, where it deems it necessary for the preservation of the unity of the country and its territorial integrity and the on-going revolution:

a) assign any Ethiopian to participate in any field of activity;

b) make use of any means of transport and communication facilities belonging to the State, mass organization, or any entity or person;

c) make use of any store house, installations, garages, establishments, equipment, machinery or any other facilities belonging to the State, mass organization or any entity or person;

d) require the sale to it of any goods and commodities necessary for the operation;

e) to regulate the conditions of the use of the right to production, distribution and sale of any essential commercial goods.

2) The National Revolutionary Operations Command may delegate its powers under sub-article 1 of this Article to Sector Commanders.

24. *Obligation to Cooperate*

1) Any Ethiopian citizen, Government office, private organization or mass organization has the obligation to cooperate with, and participate in the operation carried on under this Proclamation.

2) Any Ethiopian citizen, Government office, private organization or mass organization has the obligation to give priority to carrying out orders of the National Revolutionary Operations Command, Sector Commander or Revolutionary Operations Coordinating Committee.

25. *Offences*

1) Any person who:

a) fails to comply with or in any manner tries to evade or evades the duty imposed on him by order or regulation issued under this Proclamation; or

b) incites, encourages or in any manner assists any other person to fail to comply with the duty imposed on him by order or regulations issued under this Proclamation,

is punishable with regorous imprisonment upto five (5) years and in more serious cases with rigorous imprisonment to life or with death.

ECLN

http://www.ethcriminalawnetwork.com/

፪/ የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ወይም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ከ፫፻፴፪ እስከ ፫፻፵፮ የተመለከቱትን ቍጥሮች የጣሰ ማንም ሰው በጦር ፍርድ ቤት ይቀጣል ። ሆኖም የግንባሩ አዛዥ ወይም እሱ የሚወክለው የጦር አዛዥ ተገቢ መስሎ ሲታየው ፤ ማናቸውም በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከሰስ ጉዳይ እንደነገሩ ሁኔታ በመደበኛ ፍርድ ቤት ወይም በልዩ ጠቅላይ ጦር ፍርድ ቤት እንዲከሰስ ለማስተላለፍ ይቻላል ።

ምዕራፍ ስድስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ፤

፳፮ ፤ የመሸጋገሪያ ድንጋጌ ፤

፩/ የአብዮትና የልማት ኮሚቴዎችን ለማጠናከር በወጣው አዋጅ ቍጥር ፩፻፲፭/፲፱፻፷፱ ዓ. ም. መሠረት በወረዳ ፤ በአውራጃና በክፍለ ሀገር የአብዮትና የልማት ኮሚቴዎች ተጀምረው የነበሩት ጉዳዮች በዚህ፤ አዋጅ መሠረት በየደረጃው ለተቋቋሙት የወረዳ የአውራጃና የክፍለ ሀገር የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴዎች ተዙረዋል ።

፪/ የአብዮትና የልማት ኮሚቴዎችን ለማጠናከር በወጣው አዋጅ ቍጥር ፩፻፲፭/፲፱፻፷፱ ዓ. ም. መሠረት በማዕከላዊ የአብዮትና የልማት ኮሚቴ የተጀመሩ ሆነው ፤

ሀ/ ዘማችን የሚመለከቱ ጉዳዮች ለብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ ጽሕፈት ቤት ለውሳኔ ይቀርባሉ ፤

ለ/ ልማትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ለአገር አስተዳደር ሚኒስቴር እየቀረቡ ሚኒስቴሩ ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር እንዲፈጽሙ ያደርጋሉ ።

፳፯፤ ተፈጻሚ የማይሆኑ ሕጎች ፤

፩/ የማሻሻያው አንቀጽ እንደተጠበቀ ሆኖ የአብዮትና የልማት ኮሚቴዎችን ለማጠናከር የወጣ አዋጅ ቍጥር ፩፻፲፭/፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ተሽሯል ።

፪/ ማናቸውም ይህን አዋጅ የሚቃረኑ ሕጎች ፤ ደንቦች፤ ውሳኔዎችና ጥያቄዎች ይህን አዋጅ ለሚመለከቱ ጉዳዮች ተፈጻሚ አይሆኑም ።

፳፰ ፤ አዋጁን ስለማስፈጸም፤

ብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ ፤ የእዝ አዛዥ፤ የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ ፤ ማስታወቂያ ወይም መመሪያ በማውጣት ፤ ወይም ትእዛዝ በመስጠት ይህን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል ይችላል ።

፳፱ ፤ ደንብ የማውጣት ሥልጣን ፤

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፰ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ ይህን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም ደንብ ለማውጣት ይችላል ።

፴ ፤ አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከነሐሴ ፳፩ ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፩ ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ. ም.

ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ

2) Any person who acts in violation of sub-article 1 of this Article or Articles 332-346 inclusive of the Penal Code shall be tried by the courts martial. However, the Sector Commander or any military Commander delegated by him may, where he deems it necessary, refer any case falling under this Proclamation to the ordinary courts or the special General Court Martial, as may be appropriate.

Chapter Six
MISCELLANEOUS PROVISIONS

26. *Transitory Provisions*

1) All matters pending before the Woreda, Awradja and Provisional Revolution and Development Committees under the Revolution and Development Committees Consolidation Proclamation No. 115/1977 are hereby transferred to the Woreda, Awradja and Regional Revolutionary Operations Coordinating Committees established at every level under this Proclamation;

2) a) all matters relating to participants of operations pending before the Central Revolution and Development Committees under Revolution and Development Committees Consolidation Proclamation No. 115/1977 shall be referred to the office of the National Revolutionary Operations Command for decision;

b) all matters relating to development pending before the Central Revolution and Development Committees under Revolution and Development Committees Consolidation Proclamation No. 115/1977 shall be referred to the Ministry of Interior which shall, in consultation with the appropriate offices, ensure their implementation.

27. *Inapplicable Legislation*

1) Subject to the amendment Article, the Revolution and Development Committee Consolidation Proclamation No. 115/1977 is hereby repealed.

2) No law, regulations, decision or claim shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, have force or effect with respect to situations provided for by this Proclamation.

28. *Implementation of this Proclamation*

The National Revolutionary Operations Command, Sector Commanders or the Revolutionary Operations Coordinating Committee may implement this Proclamation by issuing notices, directives or orders.

29. *Power to Issue Regulations*

Subject to Article 28 of this Proclamation, the National Revoluionary Operations Command may issue regulations for the proper implementation of this Proclamation.

30. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of 27th August, 1977.

Done at Addis Ababa, this 27th day of August, 1977.

THE PROVISIONAL MILITARY ADMINISTRATION COUNCIL

ECLN

http://www.ethcriminalawnetwork.com/